# ሽል እንዳለ ቢቀር

የተዋህዶ ልጅ ፣ ልብ አድርገህ ስማ
በህልውናህ ላይ ፣ አንዣቧል ጨለማ
መናፍቅ ነው ያለው ፣ ከሰልጣኑ ማማ
ላውሬው ሊያስረክባት ፣ ኦርቶዶክስ ተዳክማ
ውጊያው ተጀምሯል ፣ በሰንደቅ አላማ
በእምነትህ ፀንተህ ፣ ቅለጥ እንደሻማ
በእምነትህ ዋልታ ፣ በእምነትህ አውድማ
ሌጊዮን ሰልጥኗል ፣ ነፍስህን ሊቀማ ።

በፈጣሪ መንገድ ፣ የተራመዱትን
ጌታችን አክብሮ ፣ ከፍ ከፍ ያሉትን
ክብር የማይሰጡ ፣ ቤዛዊት እናትን
ፃድቃን ሰማዕታት ፣ አዛውንት አባትን
እንደተራ ነገር ፣ የሚያዋርዱትን
እነሀ ጉግ ማንጉጎች ፣ ባገር የፈሉትን
ለማየት የሚሹ ፣ የኦርቶዶክስ ሞትን
የአርዮስ ልጆች ፣ የእሳት እራትን
አጥብቀህ ተዋጋ ፣ ሳትፈራ ሞትን ።

ባዋጅ ተጀምሯል ፣ ግልፅ ጦርነቱ
ጫና ቢበረታም ፣ ቢከፋም ግፊቱ
አይለው ቢታዩ ፣ በኃይል በጉልበቱ
ሰቆቃው ቢበዛ ፣ ስቃይ እንግልቱ
ዛሬ ቢያሳድዱህ ፣ እረተው ላይረቱ
የግድ ነውና ፣ ሊፈፀም ትንቢቱ
በመከራ ዘመን ፣ ፍቱን መድሃኒቱ
አለመወላወል ፣ በእምነት በፀሎቱ ።

ቀድሞም የምናውቀው ፣ ተዋህዶ ገድሉ
ጌታ እንዳስተማረን ፣ እንደ እምነት ወንጌሉ
ሲናወጡ መፅናት ፣ ቢያይልም ማዕበሉ
የክብርም ክብር ነው ፣ ለእምነት መጋደሉ
ጦር መሳሪያ ሳይሆን ፣ ከሁሉም ኃያሉ
የኛ አሸናፊያችን ፣ ነውና መስቀሉ ።

ይሄ ክብር ዝና ፣ ከንቱ ሆኖ ሊቀር
ከአጋንንት ጎራ ፣ ይዟት ለመደመር
ፈተናን ሊያፀና ፣ የመጣብን ባገር
ቃል እያሳመረ ፣ አሰውቦ የሚናገር
የበግ ለምድ ለባሽ ፣ የዲያቢሎስ ጨንገር
ትዕቢተኛ መሪ ፣ መቅደስ የሚዳፈር
ከፈጣሪው ጋራ ፣ ደፍሮ የሚገዳደር
ምነው እናቱ ሆድ ፣ ሽል እንዳለ ቢቀር ።

ታዛቢው

September 27, 2019